

PLAN INTERNATIONAL

አቻን መሰረት ያደረገ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃግብር:

# ‘ጉዳትን ያለማድረስ’ መመሪያ

# ይህ መመሪያ ምንድነው?

ፕላን ኢንተርናሽናል እኩዮቹን መሠረት ያደረገ መርሃ ግብርን ፣ በተለይም የአቻን ትምህርት ፣ በተለያዩ መርሃ ግብሮች እና አውዶች ውስጥ ለብዙ ዓመታት በጤና ፣ በትምህርት ፣ በጥበቃ እና በሰብዓዊ ሥራዎች ላይ ሲጠቀም ቆይቷል ፡፡ ሆኖም የእነዚህ መርሃግብሮች አሰጣጥ በከፍተኛ ሁኔታ ይለያያል። በዚህም እኛ የምንደግፋቸው በአቻ ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች በተከታታይ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ መመሪያ የመስጠትን አስፈላጊነት እንገነዘባለን ፡፡ይህ ሰነድ በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ላይ ከአቻ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መርሃ ግብሮች ዲዛይን ፣ ይዘት እና አቅርቦት ጋር የተዛመዱት ሁሉንም አደጋዎች በመቀነስ ፕሮግራማችንን ለማጠናከር ልዩ እና ተግባራዊ መመሪያን ይሰጣል ፡፡በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ዙሪያ የሚደረጉ/አሳሳቢ ውይይቶች ስሜታዊ የሚያደርጉ ርዕሶችን ስለሚይዙ በፕሮግራሞቻችን ውስጥ ያሉ ሁሉም ወጣቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ሊጎዷቸው ከሚችሏቸው ማናቸውም አደጋዎች የተጋለጡ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡

‘ጉዳት ያለማድረስ’ መርሆች ስንል ምን ማለታችን ነው?

ከፕሮግራማችን ወይም ከድርጅቱ ጋር ባለ ግንኙነት ምክንያት ማንኛውም ልጅ ወይም ወጣት ጉዳት ወይም አደጋ እንዳይደርስበት ለማረጋገጥ ፕላን ኢንተርናሽናል በሁሉም ፕሮጀክቶች ላይ ለማካተት ቁርጠኛ የሆነበት ቁልፍ መርህ ነው ፡፡ ይህ ማለት በተግባር-

- ልጆችን እና ወጣቶችን በተለይም ተጋላጭ የሆኑት ክፍሎች ለአደጋ ወይም ለጉዳት እንዳይጋለጡ የማድረግ እና የመጠበቅ ሀላፊነት አለብን ፡፡
- ሥራችንን በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ቡድኖችን ለምሳሌም (ግብረ ሰዶማዊያን + ወጣቶች ፣ በኤች አይ ቪ የተያዙ ሰዎች ፣ እርጉዝ እና ልጅ አሳዳጊ ወጣቶች) መገለልን ወይም የስርዐተ ፆታ እና ማህበራዊ ኢ-እኩልነትን ጠብቆ የሚያቆዩ ጎጂ ማህበራዊ እና የስርዐተ ፆታ ደንቦችን ባለማወቅ አያጠናክርም ወይም አያባብስም ፡፡
- ለሁሉም ወጣቶች አክብሮት ፣ አዎንታዊ እና ሁሉን አካታች ቋንቋን መጠቅምን ማረጋገጥ እና በስርዓተ ፆታ ፣ በስርዓተ ፆታ ማንነት ፣ በጾታ ዝንባሌ እና / ወይም የአካል ጉዳት ፣ የዘር ወይም የጎሳ ፣ የወሲብ እንቅስቃሴ ወይም ሌላ ማንኛቸውንም በማንነት ላይ የተመሰረቱ አድልዖዊ መልዕክቶችን ፣ማስወገድ
- የፕሮግራም ይዘት እና ቋንቋ በተመለከተ አወንታዊ የወሲብን ገጽታን እና በማስረጃ ላይ የተመሠረተ አቀራረብን መከተል ፣ በፍርሃት እና በስጋት ላይ የተመሰረቱ መልዕክቶች ማስወገድ

የፕላን ኢንተርናሽናል በአቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብሮች ‹ ጉዳት አለማድረስ› መርሆዎች ምንድናቸው?

ይህ መመሪያ በስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር የተለያዩ ደረጃዎች እና ክፍሎች የወጣቶችን ደህንነት ለመጠበቅ እና ጉዳt እንዳይደርስባቸው አደጋን ለመቀነስ ተግባራዊ አስተያየቶችን ያስቀምጣል ፡፡ በሚከተሉት 7 ደረጃዎች ከግምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮችን ይሸፍናል-

1. የፕሮግራም ዲዛይን
2. ሚናዎች እና ግዴታዎች
3. ምልመላ እና ስልጠና
4. ተስማሚ ዐውደ
5. ድጋፍ እና ቁጥጥር
6. ደህንነት እና የደህንነት ጥበቃ
7. ግላዊነት እና ምስጢራዊነት (በበይነ መረብ ላይ ጨምሮ)




ጠቃሚ ምክር

ይህ መመሪያ በቀላሉ ለማጣቀስ እንዲመች የማጣቃለያ ዝርዝርን አካቷል ፡፡ ገጽ 7 ን ይመልከቱ ፡፡

# 1. የፕሮግራም ዲዛይን



- **በአቻ ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች ጠንካራ ትስስርን ከሚያካትቱ ለወጣቶች ተስማሚ እና የስርዓተ ጾታ ምላሽ ከሚሰጡ ሰፊ መርሃ ግብር አንድ አካል ሆኖ መተግበሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።** በአቻላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር በተናጥል ሊተገበር አይገባም። በአካባቢው ያሉ አጠቃልይ ድጋፎች እና አገልግሎቶች (ለምሳሌ የቤተሰብ እቅድ ፣ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ፣ ኤች አይ ቪ ፣ የልጆች ጥበቃ እና ስርዓተ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች) አሰሳ እና የጥራት ምዘና ጥናት እንዲያኪያሂዱ አቻዎችን ማካተት አስፈላጊ የመጀመሪያ እርምጃ ነው ፡፡ ይህም ተሳትፊዎችን ወደነዚህ አግልግሎቶች ለመላክ እና ስለሚሰጡ ግልጋሎቶች ጥራቱ እንዲተማመኑ ይረዳቸዋል።እነዚህ አገልግሎቶች በአካባቢው ከሌሉ ወይም ጥራት ከሌላቸው - ወጣቶቹን ወደ እንደዚህ አይነት አገልግሎቶች በመላክ ተገቢ ያልሆነ አግልግሎት እንዲያገኙ ሊዳርጉ ይችላሉ። ይህም የበለጠ ጉዳት ሊያስከትል እና የፕሮግራሙን እና የአቻዎችን ተዓማኒነት ሊያሳጣ ይችላሉ ፡፡



- **አቻዎች በተገቢው ስርዓት (ቶች) ውስጥ በተገቢው እንዲዋሃዱ እና አስፈላጊውን የባለሙያ ምክር እና የጉዳይ አስተዳደር ድጋፍን እንዲያገኙ ከጤና ፣ ከትምህርት እና ከማኅበራዊ እንክብካቤ ዘርፎች ጋር አብሮ መሥራት ያስፈልጋል** ።አቻዎች በተናጥል እንዲሰሩ አይጠበቅም ነገር ግን ውይይቶችን በማዘጋጀት እና ስለጉዳዮች አያያዝ የምክር ፣ መመሪያ እና ድጋፍ ከሚሰጡ ከሠለጠኑ ባለሙያዎች ሥራቸውን ለማስተዳደር ተጨማሪ ድጋፍ ይፈልጋሉ ፡፡




- **አቻዎች የሥራ ድርሻቸውን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስፈልገውን የባለሙያ ድጋፍ እና የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ በጀት መመደብ ያስፈልጋል ፡፡** ይህም በጀት አቻዎች መመሪያ እና የጉዳይ አስተዳደር ድጋፍን ለመስጠት እንዲችሉ፣ ከአቻዎች ጋር መደበኛ ውይይቶችን ለሚያቀርቡ ለሠለጠኑ ባለሙያዎችን ለመክፈል; ለአቻዎች ድጎማ/አበል ለመክፈል; እና በስራቸው ውስጥ የሚከሰቱ ሁሉንም የገንዘብ ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስችል በቂ በጀት ነው ፡፡ በችግሮች ትንተና እና በፕሮግራም ዲዛይን ወቅት የተለዩ ጉዳዮችን ለመፍታትም በጀት ያስፈልጋል። ለምሳሌ መምህራን የተሟላ የሰነ ወሲብ ትምህርት ይዘትን እና የአሠራር ዘዴዎችን እንዲያቀርቡ ለማሠልጠን የገንዘብ ሀብቶችን ኢንቬስት ማድረግ በተደጋጋሚ ተለይቶ የሚታወቅ ፍላጎት ነው ፡፡



- **ፕሮግራሙን ከመተግበሩ በፊት ተጋላጭ/ስሜታዊ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮችን እና ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመለየት የአደጋ ግምገማን ማካሄድ እና የጉዳት ስጋቶችን ለመቀነስ ምላሾችን / እርምጃዎችን መስማማት ያስፈልጋል ፡፡** እነዚህ ጉዳዮች በአቻዎች ሥልጠና ውስጥ መቅረብ አለባቸው። ይህ ሲሆን አቻዎች ሊከሰቱ ለሚችሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ያውቃ።ለምሳሌ የፕሮግራሙ ተሳታፊ ሕገ-ወጥ ሊሆኑ በሚችሉበት አገር በግብረ ሰዶማዊነት ወይም ፅንስ ማስወረድ ጉዳዮች ላይ ድጋፍን የሚፈልግ ከሆነ ፡፡



- **የህብረተሰቡን ድጋፍ ለማረጋገጥ እና አላስፈላጊ ተቃዉሞ እና የጉዳት አደጋን ለመቀነስ በፕሮግራሙ ውስጥ ከሚሳተፉ ወላጆች / አሳዳጊዎች እና ግለሰቦች ስምምነት መፈለግ ይገባል ፡፡** በአቻዎች ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር ብዙውን ጊዜ ስሜታዊ የሆኑ ርዕሶችን ያጠቃልላል ፡፡ ይህም ከህብረተሰቡ እና በተለይም ከወላጆች / አሳዳጊዎች ጋር መተማመንን ለመፍጠር ፣ የፕሮግራሙን ዓላማ ለማስረዳት እና ስምምነት ለማምጣት፣ የፕሮግራም አቅርቦትን ለመደገፍ እና የህብረተሰቡን ተቃውሞ ለመቀነስ ወሳኝ ነው።


## 2. ሚናዎች እና ግዴታዎች



- **በአቻዎች ላይ የሚጫኑ ሀላፊነቶች እና ግምቶች ከጊዜ እና ስፋት አንጻር ተጨባጭ መሆናቸውን ማረጋገጥ ፡ ፡ወጣቶችን በደንብ ለማቅረብ ያልዘጋጁባችውን ዝርዝር ሙያዊ ይዘት እንዲያቀርቡ በመጠበቅ ለአደጋ ተጋላጭ ማድረግ አይገባም። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ያልተፈለገ ምላሽ/ ተቃውሞ የሚያስከትሉ እና አቻዎችን ለአደጋ እና ለጉዳት ሊያጋልጡ የሚችሉ ስሜታዊ ርዕሶችን ሊያካትቱ ይችላሉ ፡፡**አቻዎች የሰለጠኑ ባለሙያዎች ባለመሆናቸው ምክንያት እነሱ እንዲሸፍኗቸው የሚገቡ ተገቢ እና ውጤታማ የሆኑ ርዐሰ ጉዳቶችን በጥንቃቄ ማጤን አለብን ፡፡አቻዎች በሌሎች እና ደጋፊ የፕሮግራም መርሃ ግብሮች ላይ መገንባት አለባቸው። እንዲሁም ተገቢ አቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር መረጣ መርሃግብሩ ሊያሳካቸው በሚፈልገው ውጤት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ፡፡ ለበለጠ ዝርዝር መረጃ በአቻ ላይ የተመሠረተ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች መርሃ ግብር መመሪያን ይመልከቱ ፡፡



- **በመምህራን / ሌሎች ባለሙያዎች እና አቻዎች መካከል ባለው ሚና መካከል ግልጽ ልዩነት ያድርጉ ፡፡ እንደ መምህራን ወይም የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ባሉ በሰለጠኑ ባለሙያዎች በተሻለ የሚተገበሩ እንቅስቃሴዎችን አቻዎች እንዲደግሙት ማድረግ ተገቢ አይደለም** ፡፡አቻዎች የአስተማሪዎችን ቦታ በመውሰድ በክፍል ወስጥ ተማሪዎችን እንዲያስተምሩ ሊጠበቁ አይገባም ፡፡ያለ ሙያዊ ድጋፍ ወይም አስተማሪ ባልተገኘበት ሁኔታ ወይም አስተማሪዎች የትምህርት ይዘቱን ባልወደዱበት ቦታዎች ክፍተት ለመሙላት ያልሰለጠኑ አቻዎችን ብዛት ያላቸውን ወጣት ቡድኖችን እንዲመሩ መጠየቅ ሀላፊነት የጎደለው እና ትክክለኛ የአቻዎች ትምህርት መርሆ አይደለም ፡፡በትምህርት ቤቶች ውስጥ ሲ.ኤስ.ኢን ለመስጠት የሰለጠኑ እና በራስ የሚተማመኑ መምህራን ከሌሉ ድርጅቱ በአቻ ትምህርት ምትክ ይህንን ክፍተት ለመቅረፍ በመምህራን ስልጠና ላይ ኢንቬስት ማድረግ አለባቸው ፡፡በአግባቡ ድጋፍ ያላገኙ አቻዎች ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ባልሆኑበት ወይም መረጃ ባልተሰጣቸው ርዐሰ ጉዳዮች ላይ እራሳቸውን መረጃ ሲሰጡ ሊያገኙ ይችላሉ። ስለዚህም መልሶቹን በማያውቋቸው ጉዳዮች ላይ መልሶችን ለመስጠት ግፊት ሊሰማቸው ይችላል ፡፡ይህ በአቻዎች ላይ መተማመንን የሚሸረሽር፣ ሌሎች ጎጂ ውጤቶችን ሊያስከትል የሚችል እና የተሳሳተ መረጃን ወደ ማሰራጨት ሊያመራቸው ይችላል ፡፡




- **አቻዎችን አዎንታዊ አርአያ እንዲሆኑ ይደግፉ። ከፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችለውን ኃይል/ስልጣን ይገንዘቡ እና ስልጣናቸውን በሃላፊነት እንዲጠቀሙ ያረጋግጣሉ** ፡፡አቻዎች በዚህ ሁኔታ ኃይል እና የተለየ ቦታ ስላላቸው ሁ ሀብቶችን እና የመረጃ ተደራሽነቶችን ለብቻ መያዝ ይችላሉ ፡፡አቻዎች ጎጂ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችለውን ይህን ኃይል አግባብ ባልሆነ መንገድ አለመጠቀማቸውን ያረጋግጡ ፣ ለምሳሌ የእነሱን አመለካከት በሌሎች ላይ ለመጫን በመሞከር ወይም ግብዓትን በተመለከተ አላግባብ መደራደርን ፡፡

## 3. ምልመላ እና ስልጠና






- **እጩዎችን ለመመልመል ጥብቅ እና ግልጽ ሂደቶችን ለመጠቀም ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም እጩዎችን ከመምረጥዎ በፊት የሚያውቋቸውን ሰዎች መጠየቅ እና የደህንነት ማረጋገጫ ማድረግን የጠይቃል** ፡፡አቻዎች ለዚህ ሥራ ያላቸውን ተነሳሽነት ለመወያየት እና እንደ ስርዓትፆታ ፣ አካል ጉዳተኝነት እና / ወይም ዘር ባሉ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አመለካከት ለመመርመር ቃለ-መጠይቅ ማድረግን ይጠይቃል። ፡፡ በቅጥሩ ሂደት ወስጥ ስኬታማ ላልሆኑ ወጣቶች ይህ በብቃት ላይ የተመሠረተ ሂደት መሆኑን ይግለጹ። እንዲሁም እድገታቸውን ለማበረታታት እና ለመደገፍ ግብረመልስ መሰጠቱን ያረጋግጡ ፡፡የተለያዩ ወጣቶችን ለመድረስ የተለያዩ አስተዳደግና እና ልምዶች ያላቸውን እኩያዎችን ይመልመሉ ፡፡አቻዎች በሚመርጡበት ጊዜ በስርዓተ ጾታ ፣ በጾታ ዝንባሌ ፣ በዘር ፣ በአካል ጉዳተኝነት ፣ በወላጅነት ሁኔታ እና / ወይም በሌሎች ልዩነቶች ምክንያት ልዩነት አያድርጉ ፡፡



- **ጥልቀት ያለው የመጀመሪያ ሥልጠና ተከታታይ ስልጠናዎችን መስጠት ፡፡** አቻዎች በተቻላቸው አቅም ሁሉ የድርሻቸውን ለመወጣት ፣ ትክክለኛ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ፣ የሙያ ድንበሮችን ለመጠበቅ እና የደህንነት እና የጥበቃ መመሪያን ለመከተል ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከ3-5 ቀናት አጠቃላይ ሥልጠና ቅድመ ሁኔታ ነው ፡፡

- ጥልቀት ያለው ሥልጠና ሚናዎችን እና ኃላፊነቶችን; የቲማቲክ ይዘት; እሴቶችን እና አመለካከቶችን ይመረምራል; ስለግል ወሰኖች ፣ ድጋፍ እና ቁጥጥር ያብራራል ፣ ስለ ደህንነት እና ጥበቃ; የማጣቀሻ እና የድጋፍ ስርዓቶችን ይሸፍናል።የአቻዎችን ዕውቀት እና ችሎታ መገንባት ለማስቀጠል እና በስራቸው ውስጥ የሚለዩዋቸውን ወይም በክትትል ወቅት የሚነሱትን ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ለመፍታት በመደበኛነት ‹የተሃድሶ› ስልጠና መካሄድ አለበት ፡፡በየአመቱ ቢያንስ የ 2 ቀናት ‘የተሃድሶ’ ሥልጠና የሚመከር ሲሆን ይህም እንደ አንድ የተጠናከረ ሥልጠና ወይም እንደ ሁለት የአንድ አንድ ቀን ሥልጠናዎች ሊሰጥ ይችላል ፡፡በትኩረት ያለው ስልጠና ቀጣይነት ባለው የባለሙያ ቁጥጥር እና ድጋፍ ይታገዛል ፡፡


## 4. ተገቢ ይዘት



- **ዝርዝር ሙያዊ ወይም ጤናን የተመለከቱ ይዘቶችን ያስወግዱ - አቻዎች ለምሳሌ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለሚተላለፉ/የአባላዘር በሽታ ምልክቶች ላይ ክፍለ-ጊዜዎችን መስጠት ወይም በወሲባዊ ጥቃት እና ብዝበዛ ላይ ውይይቶችን ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም ፡፡** ይህ በወጣቶች ላይ ከእውነታው የራቁ ነገሮችን መጠበቅን የሚያመለክት ሲሆን ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ወይም ጎጂ መልዕክቶች እንዲተላለፉ ሊያደርግ ይችላል ፡፡አቻዎች በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ባለሙያ መሆን የለባቸውም ነገር ግን ከወጣቶች ጋር ውይይቶችን ማበረታታት፣ ማመቻቸት እና ወደ ስፔሻሊስት/ልዩ አገልግሎቶች ማስተላለፍ መቻል አለባቸው ፡፡በወጣቶች መብቶች እና ስምምነት ይዘት ላይ-ያተኮረ እና ወጣቶች በጾታ እና በግንኙነቶች ዙሪያ ስላላቸው አመለካከት እና እሴቶች እንዲያስቡ ለማገዝ የሚረዱ እንቅስቃሴዎች; አደጋን መመርመር እና መገምገም; እና ውሳኔ አሰጣጥን የሚደግፉ ክህሎቶችን ማዳበር ፣ በራስ መተማመን እና ለራስ ከፍ ያለ ግምትን ስለመውሰድ ያሉ ርዕሶች አቻዎች ለኩዮቻቸው ማድረሳቸው ይበልጥ ተገቢ ይሆናል ፡፡



- **የአቻ መመሪያዎች እና ሰነዶች የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ይዘት ሁሉን አካታች ከሆነው የስነ ወሲብ ትምህርት ላይ ካለው የፕላን የጥራት ደረጃዎች ጋር የሚስማማ መሆኑን ማረጋገጥ ፡፡ ከድርጅታዊ እሴቶች እና አቋሞች ጋር የሚቃረኑ እና ትክክለኛ ያልሆኑ እና / ወይም ጎጂ መልዕክቶችን የሚያካትቱ የአቻዎች ብሔራዊ ሥርዓተ-ትምህርት መርሃ ግብሮች - ለምሳሌ መታቀብ ላይ የተመረኮዙ መልዕክቶችን ማስተዋወቅ ወይም ስለ ግብረ ሰዶማዊነት አድልዎ የሚያደርጉ መልዕክቶችን ጨምሮ - ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም ፡፡**ይዘቱ አወንታዊ ወሲብን ፣ ለወጣቶች ሕይወት ጠቃሚ ፣ አካታች እና ፍርሃትን ፣ ወቀሳዎችን እና / ወይም አድሎአዊ መልዕክቶችን ማስወገድ አለበት ፡፡.




- **ይዘቱ ለተለያዩ የዕድሜ ቡድኖች ተስማሚ መሆኑን ያረጋግጡ ፡፡** ዕድሜያቸው ከ10-14 ለሆኑ ሕፃናት ተስማሚ የሆነ ይዘት በዕድሜ ለሚበልጡ ጎረምሳዎች ከሚመጥናቸው ውይይቶች የተለየ መሆን አለበት ፡በተመሳሳይ ከፍ ላሉ ጎረምሳዎች የተዘጋጀ ይዘት ለትንንሽ ልጆች ምቾት የማይሰጡ እና ጭንቀት የሚፈጥሩ ርዕሶችን ወይም ሁኔታዎችን ሊያቀርብ ይችላል




- **አቻዎች ስራቸውን ለመደገፍ የሚጠቀሙባቸውን ግልፅ እና ቀላል መረጃዎችን ያቅርቡ ፣** ለምሳሌም ፍላሽ ካርዶችን ፣ ስዕሎችን ከጥያቄዎች ጋር ፣ ቀላል ክፍለ ጊዜዎች እና የፈጠራ እንቅስቃሴዎች እና / ወይም በጨዋታዎችን ያካትታል ፡፡አቻዎች ሥራቸውን የሚደግፉበት ተገቢ እና የታመኑ መረጃዎች/ሰነዶች ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይገባል። እነሱ የሚያቀርቡት መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ እና የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ፕሮግራሞችን ወጤታማ እንዲሆኑ ይህን ማድረግ አስፈላጊ ነው ፡፡

## 5. ድጋፍ እና ቁጥጥር





- **አቻዎች በሚያደርጓቸው ውይይቶች እና ለሌሎች ወጣቶች በሚሰጡት ድጋፍ ተገቢውን የሙያ ድንበር መያዛቸውን ማረጋገጥ ፡፡** አቻዎች ሁሉንም መልሶች እንዲያውቁ ወይም ሁሉንም ጉዳዮች 'እንዲፈቱ' አይጠበቅባቸውም ፤ ተጠቃሚዎች በአቻዎች ላይ ከመጠን በላይ ጥገኝነት ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይህም አቻዎችን ተገቢ ያልሆኑ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲደክሙ እና እንዲጨነቁ ያደርጋቸዋል ፡፡አቻዎች ሊሰጧቸውን የሚችሏቸውን የድጋፍ ውስንነቶች ተረድተው አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ወጣቶችን ወደ ሌሎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንዲያስተላልፉ ማድረጉ በጣም አስፈላጊ ነው ፡፡ይህ በማንኛውም አቻዎች ላይ የተመሠረተ ሥልጠና አስፈላጊ አካል ነው ።



- **አቻዎች በስራቸው ላይ የሚያወጡትን ወጪ ሁሉ ለመሸፈን የገንዘብ ድጋፍ ይስጡ ፡፡**አቻዎች ክፍለ-ጊዜዎች ወይም ስልጠናዎችን ለመከታተል የራሳቸውን ገንዘብ እንዲጠቀሙ አይጠብቁ ፡፡በጎ ፈቃደኝነታቸውን ያለ አግባብ ላለመጠቀም ይጠንቀቁ። ለሥራቸው ዕውቅና ለመስጠት ድጎማ ይስጡ። ያለ ክፍያ አቻዎች ለመቆየት ይቸገራሉ። የትራንስፖርት ፣ የስልክ ወጮዎችን እና በደንበኞቻቸው የሚፈለጉትን ቁሳቆሶችን ለመሸፈን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል ፡፡



- **ወጣቶች ከሚደርሷቸው ወጣቶች አቻዎች ጋር ተመሳሳይ ተግዳሮቶችን ፣ ተጋላጭነቶች ፣ አደጋዎች እና የድጋፍ ፍላጎቶች እንዳሏቸው በማወቅ ፕላን ኢንተርናሽናል እነዚህ ፍላጎቶች ምላሽ የመስጠት እና አቻወችን ‹የመንከባከብ ግዴታ› አለበት ፡፡**አቻዎች ለሚሠሩበት ፕሮግራም ተሳታፊዎች ሁኔታዎችን እና ልምዶችን ይጋራሉ እናም ለጤና ጉዳዮች ፣ ህክምና ፣ ቀጠሮዎች እና የምክር አገልግሎት የራሳቸውን ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ ፡፡



- **ለአቻዎች ቀጣይነት ያለው የሙያዊ ድጋፍ እና ቁጥጥር ያቅርቡ ፡፡**አቻዎች የመደበኛ ክፍለ ጊዜዎችን በመጠቀም የሚያሳስቧቸውን ነገሮች ለመጋራት ፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመወያየት እና ልምምዳቸውን ለማሻሻል ተገቢውን ድጋፍ እና መፍትሄዎችን ለማግኘት ይረዳቸዋል ፡፡የሚፈለገው ድጋፍ በመርሃ ግብሩ ድግግሞሽ ላይ የተመረኮዘ ነው ፣ ለምሳሌ አቻዎች በየቀኑ ከፍተኛ ድጋፍ የሚሰጡ ከሆነ የሙያ ቁጥጥር እና የድጋፍ ክፍለ ጊዜዎች በየሳምንቱ መሰጠት አለባቸው ፣ ሳምንታዊ ስብሰባዎችን የሚያቀርቡ አቻዎች ግን አነስተኛ ተደጋጋሚ ድጋፍ ይፈልጋሉ (ለምሳሌ በየወሩ) ፡፡



- **የአቻዎች ተቆጣጣሪዎች (ለምሳሌ የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ፣ መምህራን) የፕላን ኢንተርናሽናል የጥበቃ ፖሊሲን በሚያከብር መንገድ ለአቻዎች ግብረመልስ እና ድጋፍ መስጠታቸውን ማረጋገጥ ፣ ለምሳሌ ምስጢራዊነትን ማክበር እና አድልዎ እና ቅጣትን ማስቀረት ፡፡**አቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብርን ይዘት እና አሰጣጥን በተከታታይ ለማሻሻል እና ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ እና ያልተፈለገ አደጋን ለመቀነስ እንዲሁም የአቻዎችን ደህንነት ለመከታተል የአቻዎችን ተግባር መከታተል፣ቁጥጥር እና ድጋፍን ማድረግ አስፈላጊ ነው ፡፡

## 6. ደህንነት እና የደህንነት ጥበቃ



- **የአቻዎችን እና የፕሮግራም ተሳታፊዎችን ደህንነት ማረጋገጥ ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው ፡፡** በተወሰነ አውድ ውስጥ በጣም ስሜታዊ ሊሆን የሚችል ይዘትን እንዲያቀርቡ አይጠይቁ ፣ ገዳቢ ሁኔታዎች ውስጥ ለምሳሌ እንደ ግብረ ሰዶማዊነት ወይም ፅንስ ማስወረድ ባሉ ጉዳዮች ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶች አሉታዊ ወይም ጎጂ ውጤቶች ሊያስከትሉ በሚችሉ ፡፡ለአስቸጋሪ ሁኔታዎች እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚችሉ (ለምሳሌ ፣ አንድ የፕሮግራም ተሳታፊ ጽንስ ማስወረድ ህገ-ወጥ በሆነበት ሀገር ውስጥ ስለ ፅንስ ማስወረጃ አገልግሎቶች ከጠየቀ) እነዚህ መሰል ጉዳዮች የሥልጠና አስፈላጊ አካል መሆን አለባቸው። እናም በሚደረገው የአደጋ ግምገማ ላይ መታየት አለባቸው




- **አቻዎች ያለምንም እንግልት እና / ወይም አደጋ ተግባራቸውን የሚያከናውንበት አስተማማኝ ቦታ ይስጡ ፡፡** የአቻዎች ደህንነትን የሚያረጋግጡ ተጨማሪ የደህንነት ዘዴዎችን ያዘጋጁ ፣ ለምሳሌ ተገቢ በሆነ አውድ ወስጥ ጥንድ ሆነው መሥራት እና አቻዎች ከስራ ሲመለሱ 'ተመዝግቦ የመግባት' ስርዓትን መዘርጋት የመሳሰሉትን ማካተት።በልብስ እና በቦርሳዎች ላይ ማስተዋውቅን በጥንቃቄ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህ ምንአልባትም ግለሰቦች ተለይተው እንዲታወቁ እና ኢላማ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል። ለምሳሌ ሳያውቁ የኤች.አይ.ቪ ሁኔታን ማሳወቅን የመሳሰሉን ያካትታል። እንዲሁም አቻዎች ሥራ የሚሠሩበትን ጊዜ እና ቦታ ግምት ውስጥ ያስገቡ ፡፡ አንዳንድ ቡድኖችን ለመድረስ ምን አልባትም በሌሊት መሄድን ወይም ወይም ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸውን አካባቢዎች መጎብኘትን ሊጠይቅ ስለሚችል ተገቢ የጥበቃ አሰራሮች በቦታው መኖር አለባቸው ፡፡



- **በጥላን ኢንተርናሽናል የጥበቃ መመሪያ መሠረት ክጥሰቶች ስለመጠበቅ እና ጥሰቶችን ሪፖርት ስለማድረግ ለአቻዎች ግልጽ እና የሰነድ መመሪያ መኖሩን ማረጋገጥ ፡፡** ይህ የማንኛውም የአቻ ሥልጠና እና ሽፋኖች ቁልፍ አካል ነው ፣ ለምሳሌ የቋንቋ አጠቃቀም ፣ በግለሰባዊ ግንኙነቶች ላይ ያሉ ድንበሮች ስለመጠበቅ እና ስጋቶችን ሪፖርት የማድረጊያ ስልቶችን ያካትታል ፡፡

## 7. ግላዊነት እና ሚስጢራዊነት (በበይነ መረብ ላይ ጨምሮ)



- **በበይነ መረብ ላይ የአቻዎች እና ወጣቶች ግላዊነት እና ምስጢራዊነትን ለማረጋገጥ ተጨማሪ የደህንነት ዘዴዎችን ይተግብሩ።** በ "ኮቪድ -19" ወረርሽኝ ምክንያት አንዳንድ በአካል የሚደረጉ ስብሰባዎች አሁን በበይነ መረብ መስመር ላይ እየቀረቡ ይገኛሉ። ይህም የወጣቶችን ደህንነት እና ጥበቃን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ትኩረት ይፈልጋል ፡፡ይህ ምናልባት ተጋባዥ ቡድኖች እና ስብሰባዎችን በማካሄድ ወይም የይለፍ ቃላትን መጠቀም ሊሆን ይችላል። በውይይት እና ጥያቄዎች ላይ የሚሳተፉ አቻዎች ተለይተው እንዳይታወቁ ቅጽል ስሞችን መጠቀም ይችላሉ ፡፡ በተለይም ወጣቶች ውይይታቸውን ከሚያካፍሉ ሰዎች ጋር ስልኮችን ወይም ኮምፒተርን የሚያጋሩ ከሆነ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው



- **በበይነ መረብ መስመር ላይ ያሉ ግንኙነቶችን ጥበቃ ማድረግን በተመለከተ አቻዎች ሙሉ በሙሉ መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ፡፡** ሁሉም ተሳታፊዎች በበይነ መረብ መስመር ላይ በጋራ/ በቡድን መማር እና መስተጋብር ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን ለምሳሌ እንደ መከባበር ፣ የቋንቋ አጠቃቀም ፣ የተወሰኑ የግል መረጃዎችን አለመጋራትን፣ እና ምስጢራዊነትን ማክበር በመሳሰሉት ላይ ግልጽ መመሪያ ያስፈልጋቸዋል ፡፡



# የማረጋገጫ ዝርዝር ማጠቃለያ


የሚከተሉት ጥያቄዎች በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብር ከመተግበሩ በፊት እና / ወይም ፕሮግራም ሲገመገም እንደ ማረጋገጫ የሚያገለግሉ ዝርዝር ነው ፡፡ጥያቄዎቹ ምሉዕ አይደሉም ስለሆነም እንደየ አውዱ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልግ ይሆናል ፡



**1.** ፕሮግራምዎ በአቻዎች ላይ የተመሠረተ መርሃ ግብርን በተሳካ ሁኔታ ለማድረስ **ደጋፊ ድባብን** ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ነጥቦችን አካቷልን?መርሃ ግብሩ የማህበረሰብ ድጋፍ አለው?አግባብነት ያላቸው ፈቃዶች እና መስማማቶች ተገኝተዋል? አቻዎች ላይ የተመሰረቱ መርሃ ግብሮች ለወጣቶች ተስማሚ እና ለስርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጭ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች አገልግሎቶችን ተደራሽነት እና ማጣቀሻዎችን ያካተተ ሰፊ የፕሮግራም አካል ሆኖ እየተሰጠ ነውን?



**2.** በፕሮግራሙ ውስጥ ለአቻዎች የተሰጡት **ሚናዎች እና ኃላፊነቶች** ተገቢ ናቸውን? አቻዎች ሙሉ በሙሉ ተዘጋጅተዋል? ድጋፍስ አግኝተዋል? ሌሎች ባለሙያዎችን ከመተካት ይልቅ አብረው እየሠሩ ናቸው? አቻዎችን ለመደገፍ የሚያስችል ሥልጠና እና ቀጣይነት ያለው የአመራር ፣ የቁጥጥር እና የድጋፍ ሥርዓቶች አሉ? አቻዎች ወጪዎቻቸውን ለመሸፈን እና / ወይም ድጎማ ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ አላቸው?



**3.** የአቻዎች ሥራ በድርጅቱ እና **በአገልግሎቶች የተደገፈ ነውን?** ጉዳዮችን ለማስተዳደር አቻዎች የባለሙያ ቁጥጥር እና መመሪያ እያገኙ ነው? በአካባቢ የሚገኙ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶችን እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን (ለምሳሌ ስርዓተ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እና የልጆች ጥበቃ አገልግሎቶችን) ለመለየት ከወጣቶች ጋር በመተባበር የአሰሳ ስራ ተካሂዷልን? ውጤታማ ትስስር እና ሪፈራል/የማስተላለፍ ስርዓትስ ተቋቁመዋል?



**4.** አቻዎች እያቀረቡት ያለው **ይዘት** ተገቢና ትክክለኛ ነው?ብዙ ዝርዝር ሙያዊ ይዘቶችን እያቀረቡ ነው? አቻዎች የወጣቶችን መብቶች በሚመረምሩ ፣ አደጋን የሚገመግሙ እና የተግባቦት እና በራስ የመተማመን ክህሎቶችን የሚያዳብሩ አሳታፊ ውይይቶችን እያደረጉ ነው?ሥራዎቻቸውን ለማቅረብ የሚረዱዋቸው ሰነዶች/መረጃዎች አሏቸው?በሂደቱ ላይ (በምናደራጃቸው ተግባራት ፣ በምንጠቀምባቸው ስልቶች ፣ በምንሰጠው ድጋፍ) ዙሪያ መረጃዎችን እና ግብረመልሶችን በመሰብሰብ ረግርድ  እቅድ በማውጣት እና በመደገፍ ላይ አቻዎችን ያሳትፋሉ? ማንኛውንም ያገኟቸውን ትምህርቶች ይሰንዱ ዘንድ አቻዎችዎን እያገዙ ነው?



**5.** **የደህንነት እና የደህንነት ጥበቃ** ሂደቶች አሉ?አቻዎች ሥራቸውን የሚያከናውኑበት አስተማማኝ ቦታ አላቸው? በተጨማሪ የትንኮሳና የጉዳት እድልን ለመቀነስ ተጨማሪ የደህንነት እርምጃዎች ተተግብረዋልን? አቻዎች የደህንነት ጥበቃን በተመለከተ ሥልጠና አግኝተዋል? በፕላን ኢንተርናሽናል የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት የደህንነት ጥሰቶችን ምላሽ ለመስጠት እና ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ  የጽሁፍ መመሪያዎችን ማግኘት ይችላሉን? የፕሮግራም ተሳታፊዎችን የበይነ መረብ መስመር ላይ ደህንነታቸውን የሚያረጋግጡባቸውን መንገዶች ከግምት አስገብታችኋል?

PLAN INTERNATIONAL

ይህ ሰነድ በፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (ኤምኤፍኤ) የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ ነው ፡፡ የፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዚህ ውስጥ የተገለጹትን አስተያየቶች የግድ አይጋራም ፡፡ ፕላን ኢንተርናሽናል የይዘቱ ብቸኛ ኃላፊ ነው

With support from
Finland's development
cooperation

በመጀመሪያ በ 2013 ዓ.ም ታተመ

Text © ፕላን ኢንተርናሽናል 2013 ዓ.ም. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

የፕላን ኢንተርናሽናል ቅድመ ፈቃድ ሳይኖር የዚህ ጽሑፍ ክፍል በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ በኤሌክትሮኒክ ፣ በሜካኒካል ፣ በፎቶ ኮፒ ወይም በሌላ መንገድ ማባዛት ወይም ማስተላለፍ አይቻልም።

ፕላን ኢንተርናሽናል (2013). አቻን መሰረት ያደረገ የስነ ወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች: 'ጉዳትን ያለማድረስ' መመሪያ. ዩናይትድ ኪንግደም: ፕላን ኢንተርናሽናል.

ትርጉም በማህደር ተስፋ የሻው